አፍሪካ ቲቪ

18

# አፍሪካ አካዳሚ

AFRICA ACADEMY

# ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት የአጫጭር ሱራዎች አስተምህሮት

(ከሱረቱ ናስ - ሱረቱ ዱሓ)

4

በቴሌግራም

AAcademyEthio

www.AfricaAcademy.com

# سُورَةُ الفَلَقِ

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

قُلۡ أَعُوذُ بِرَبِّ ٱلۡفَلَقِ ١ مِن شَرِّ مَا خَلَقَ ٢ وَمِن شَرِّ
غَاسِقٍ إِذَا وَقَبَ ٣ وَمِن شَرِّ ٱلنَّفَّٰثَٰتِ فِي ٱلۡعُقَدِ ٤
وَمِن شَرِّ حَاسِدٍ إِذَا حَسَدَ ٥



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

# ሱረቱ አል-ፈለቅ እና ሱረቱ አን-ናስ

- (የተፈልቃቂው ምዕራፍ) የወረደው በመካ ነው፡፡ የምእራፉ አናቅፅ (5) ናቸው፡፡
- (የሰዎች ምዕራፍ) የወረደው በመካ ነው፡፡ የአናቅፁ ብዛት (6) ናቸው፡፡

## ከምዕራፉ ዓላማዎች፡-

- ሱረቱ አል ፈለቅ ግልፅ ከሆኑ ክፉ ነገሮች በአላህ መጠበቅ እና ወደ አላህ መጠጋት ወሳኝ መሆኑን የሚያስረዳ ምዕራፍ ነው።
- ሱረቱ አን ናስ ከሸይጧን ተንኮልና ጉትጎታ እንዲሁም ድብቅ ከሆኑ ተንኮሎች በአላህ መጠበቅ እንዳለብን የሚገልፅ ምዕራፍ ነው።



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

አፍሪካ አካዳሚ

# በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

- (1) አንተ መልዕክተኛ ሆይ! በንጋቱ ጌታ እጠበቃለሁ ወደ እርሱም እጠጋለሁ በል።
- (2) ከፍጡራን ሁሉ ተንኮልና ክፉ ነገር፤
- (3) በለሊት ጊዜ ከሚገኙ ነፍሳት፣ ሌቦች ወዘተ... ክፉ ነገሮች ክፋት በአላህ እጠበቃለሁ።
- (4) በተቋጠሮ ክሮች ላይ ከሚተፉት ሴት ድግምተኞች ተንኮል በእርሱ እጠበቃለሁ።
- (5) ምቀኛ በምቀኝነቱ ተነሳስቶ ከሚሠራው ተንኮልም በእርሱ እጠበቃለሁ።



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

አፍሪካ ዲናዊ እውቀት አካዳሚ
(ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት "ከሱረቱ ናስ - ሱረቱ ጧሃ")

አፍሪካ አካዳሚ

# سُورَةُ النَّاسِ

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

قُلۡ أَعُوذُ بِرَبِّ ٱلنَّاسِ ١ مَلِكِ ٱلنَّاسِ ٢ إِلَٰهِ
ٱلنَّاسِ ٣ مِن شَرِّ ٱلۡوَسۡوَاسِ ٱلۡخَنَّاسِ ٤ ٱلَّذِي
يُوَسۡوِسُ فِي صُدُورِ ٱلنَّاسِ ٥
مِنَ ٱلۡجِنَّةِ وَٱلنَّاسِ ٦



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

## በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

- (1) አንተ መልዕክተኛ ሆይ! በሰዎች ጌታ እጠበቃለሁ፣ በል።
- (2) የሰዎች ንጉሥ በሆነው፤ በነሱ ላይ የፈለገውን ነገር የሚያደርግ ከእርሱ ወጪ ሌላ ንጉሥ የላቸውም።
- (3) እውነተኛ አምላካቸው ነው። ከእርሱ ውጪ በእውነት የሚመለክ አምላክ የላቸውም።
- (4) ሰዎች አላህን ማውሳት ሲዘነጉ ውስወሳውን የሚለቅባቸውና አላህን ሲያወሱ ከሚርቀው ሸይጧን ተንኮል በአላህ ስም እጠበቃለሁ።
- (5) በሰዎች ልቦች ውስጥ ገብቶ የሚጎተጉት ከሆነው፤
- (6) የአጋንንት ሸይጧን እንዳለ ሁሉ፥ የሰው ሸይጧንም አለ።

አፍሪካ አካዳሚ

## ከሱረቱ አል ፈለቅ እና ሱረቱ አን ናስ ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-

- 1. ድግምት እና መፈወሻ ስልቱም መጠቀሱ።
- 2. የጉትጎታ መድህኒት አላህን ማውሳት እና አላህን ጥበቃን መጠየቅ መሆናቸውን።
- 3. ሼይጣን የሰው ልጆች ክፉ ጠላታቸው መሆኑን፤ መወስወስ (መሳሳት) በሰይጣን ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በእርጉም ሰዎችም ሊፈፀም እንደሚችል እና ከዚህ መሰሉ ችግር መጠበቅ የሚቻለው በአንድ አላህ ብቻ መሆኑን፤
- 4. አላህ የነብዩችና የትክክለኛ አማኞች ብቸኛ መጠጊያ መሆኑን፤
- 5. የሼይጣን ትዕዛዝ የሚያስፈፅሙ አያሌ ረዳቶች ያሉት መሆኑንም እንረዳለዐን፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com